የኢትዮጵያ ትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ ካርታ

# በቴ/ሙ/ት/ሥ ዘረፍ የለውጥ ምክረ ሀሳቦች

# የምርምር ቡድን አባላት

**የቴ/ሙ/ ንዑስ ኮሚቴ አባላት**

- ዶ/ር ብርሃኑ አሰፋ
- ዶ/ር ዳንኤል ረዳ
- ዶ/ር ጌታቸው ብሩ
- ዶ/ር መላኩ መንግስቱ
- ዶ/ር መላኩ ዋቁማ
- ዶ/ር ዋና  ሌቃ

# በቴ/ሙ/ት/ሥ ዘርፍ የታዩ ድክመቶችና ተግዳሮቶች

# ፖሊሲና እስትራቴጂ በተመለከተ የታዩ ችግሮች

- አሁን ያለው ፖሊስ ገዳቢ ከመሆኑ የተነሳ በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ውስጥ ጥራት ያለው መካከለኛና ከፍተኛ ባለሙያ ለማሰልጠን አለመቻል፤
- በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ምሩቃን ወደ ከፍተኛ የስልጠና ፕሮግራም እና ትምህርት የሚያሳደግና የሚያሸጋግር (Progression and Permeation) ሥርዓት መንደፍ የሚያስችል የፖሊሲ ድጋፍ አለመኖር፡- ይህ የቴክኒክና ሙያ ፕሮግራም የማያሳድግ ዝግ (Dead end) ተደርጎ እንዲቆጠር አድርጎታል፡፡
- እንዱስትሪና የግል ድርጅቶች ለቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የራሳቸውን የገንዘብ ድጋፍ/አስተዋጽኦ  እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ፖሊሲ አለመኖር፤
- ከእንግሊዝኛ ሌላ ሰልጣኞች በሚችሉት ቋንቋ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና መስጠትን የሚያስችል (Flexible Training Language) ፖሊሲ አለመኖር፤

# ፖሊሲና እስትራቴጂ . . .

- ጥራት ያለው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተደራሽነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የሥልጠና ተቋማትን አለማደራጀት፤
- የሀገሪቱን የኢኮኖሚ መሰረት ለሆነው ለእርሻና ግብርና ትኩረት አለመስጠት፡ – እርሻው ወይም ግብርናውን ለማዘመን እና ምርታማነት በፍጥነት ለማሳደግ የሚያስችል በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የፖሊሲ ትኩረትና የእስትራቴጂ መንደፍና መተግበር ሲኖርበት አልተሰራም፡፡
- የተለያዩ እንዱስትሪና ኢኮኖሚ ዘርፍ ተቀናጅተው ለዘርፋቸው ተገቢ፣ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያ ለማሰልጠን የሚያበረታታ ፖሊሲና እስትራቴጂ አለመኖር፤
- ሀገራዊ ፍላጎትን በሚገባ ያላገናዘበ የሥራ እስታንዳርድ (Occupational Standards – OS) ማዘጋጀት፤
- የትብብር ስልጠናን (Cooperative Training – Dual Training) ለመተግበር በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ እስትራቴጂ የታቀደው እቅድ ከሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም አለመሆን፤

# የቴ/ሙ/ት/ሥ ዘርፍ የአደረጃጀት፡ አስተዳደርና አመራር

- የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ከሚመራው/ከሚያስተባብረው ባለድርሻ አካላት እና ከሚሰራው የሥራ ስፋት፣ ጥልቀትና ብዛት የሚመጥን እና ተገቢነት ያለው የፖለቲካ፡ የአስተዳደርና የአመራር ስልጣንና አቅም የሌለው መሆኑ፤
- የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓት የሚመራው ተቋም፡ የሥራ ፈጠራ (ና የምግብ ዋስትና) እና አነስተኛና መካከለኛ እንተርፕራይዝ ማስፋፋት ኤጄንሲዎች የተሰጣቸው ኃላፊነት አቀናጅው ውጤታማ በሚሆኑት መልክ የሚመራ የበላይ የጋራ ተቋም አለመኖር፤
- የክልሎች የቴክኒክና ሙያ አስተዳደርና አመራር የአቅም ውስንነት ምክንያት ለክልሎቹ እና በውስጣቸው ላሉ ዞኖችና ወረዳዎች የኢኮኖሚ ልማት እቅዶች ጋር የሚጣጣም የሥልጠና እቅድ ማቀድና ማስፈጸም አለመቻል፤
- የሚፈለገውን የሥልጠና ደረጃ የሚመጥን ሀገራዊ የሥርዓተ–ትምህርት – ስልጠና (curriculum) እና የስልጠና መጽሐፍት (Training Materails) አለመኖር በተለያዩ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚሰጥ ስልጠና መለያየት አስተዋፅኦ ማድረጉ፤

# የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ትግበራ ጋር በተያያዘ

- ወደ ቴክኒክና ሙያ ለመካከለኛ ደረጃ ሙያ ለመሰልጠን የሚገቡ አብዛኛው ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ችሎታ ደካሞች ስለሆኑ የስልጠናው ጥራት ጉዳት እያደረሰ ይገኛል፡፡
- ጥራት (ብቃት) ያላቸው የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት እኩል ተደራሽነት ማጣት የተነሳ በተለያዩ የሀገሪቱ የሚኖሩ ዜጎች ተመጣጣኝ ብቃት ያላው ስልጠና አያገኙም፡፡
- በቴክኒክና ሙያ ስልጠና  እና በሰልጣኞች ምዘና የኢንዱስትሪ ተሳትፎ ደካማ ስለሆነ ሰልጣኞች ተገቢነት ያለው የተግባርና የእንዱስትሪ ክሕሎት ምዘና ውስንነት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡
- ከክልል ክልል ሰልጣኝ ምሩቃን የሚመዘኑበት የብቃት ምዘና ሁኔታ በጣም የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ በተመሳሳይ የሙያ ደረጃ ብቁ የተባሉትን መወዳር አለመቻል፤

# ከትግበራ ጋር በተያያዘ . . .

- በአብዛኛው በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት የሚሰጡ የስልጠና ዓይነቶች ሀገራዊ፣ ክልላዊና ቀጠናዊ ኢኮኖሚ ከሚፈልገው የሰለጠነ የሰው ኃይል ጋር የማይናበብ መሆን፤
- ተቋማት መሀከል ያለው በመምህራኖቻቸው የሚዘጋጁ ሥርዓተ–ትምህርት/ስልጠና እና የስልጠና ማቴሪያልስ መለያየት፤
- ብቁና ተነሳሽነት የላቸው የቴክኒክና ሙያ መምህራንና አሰልጣኞች እጥረት፤
- ለቴክኒክና ሙያ ስልጠና በተማሪዎች፡ በወላጆችና እና በቀጣሪዎች ያለው ዝቅተኛ አመለካከት በተማሪዎች ጥራትና ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፤

# ከቴክኒክና ሙያ ፋይናንስ ጋር በተያያዘ፡-

- ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል ጠንካራና ደጋፊ የፋይናንስ ስርዓት አመኖር፤
- እንዱስትሪና የግል ድርጅቶች ጥራት ያለው ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ለማካሔድ ተሳትፎም ሆነ የሚያደረጉት የገንዘብ ድጋፍ/አስተዋጽኦ  በጣም ውስን መሆን፤
- በመንግሰት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና የሁለት እዮሽ የመንግሰታት ትብብር የቴክኒክና ሙያ ዘርፉን ለማዘመንና ማሳደግ የተሰራው ሥራ ውስንነት፤
- ለመንግሰት ቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚመደበው በጀት ውጤታማነት ማዕከል ያደረገ  የሰልጣኞች ቁጥር እና በስልጠና ዓይነት ብዛት የሚወሰን መሆን፤
- የመንግሰት የቴክኒክና የሙያ ተቋማት አምራች እንዲሆኑና ገቢ ማመንጨት የሚያስችል እስትራቴጂ እና የአስተዳደር ሥርዓት አለመኖር፡፡

# በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የተሰጡ የለውጥ ምክረ ሃሣቦች

# ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ የተሰጡ የለውጥ ምክረ ሃሣቦች

- ዝቅተኛ የቴክኒክ ባለሙያ፣ ቴክኒሻን ፣ ቴክኖሎጂስትና የቴክኒክ መሃንዲስ ወዘተ. ለማፍራት የሚችል የቴ/ሙ/ት/ሥ ሥርዓት መዘርጋት፤

- በሙያ ደረጃ ዝግጅትና ባለቤት ሊሆን የሚችል ሙያ መሰረት ያደረገ የተደራጀ የቴክኒሻን፣ ቴክኖሎጂስትና የቴክኒክ መሃንዲስ እና ሌሎች የዕደጥበብ ባለሙያዎች ማህበራት/ቻምበር/ ለመፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤

- የቴክኒክና ሙያ ምሩቃን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ስልጠና ለመሳተፍ የሚያስችል እና ወደ ከፍተኛ የአካዳሚክ ትምህርት መግባት የሚያስችል መንገድ /pathway/ መቅረፅ፤

# ከፖሊሲ ጋር የተያያዙ . . .

- ዜጎች በራሳቸው ፍጥነትና ሚመርጡት የትምህርት ዘዴ እና ዝንባሌአቸውን መሠረት ባደረገ እንዲማሩ የሚደግፍ ፖሊሲ ማውጣት፤
- የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ውጤታማ ለማድርግ በተለያዩ የስልጠና ቋንቋዎች ለማሰልጠን የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፤
- እንዱስትሪና የግል ድርጅቶች በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሂደት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ሥርዓት መዘርጋት፤

# ስትራቴጂ ጋር የተሳሰሩ ለውጦች ምክረ ሀሳቦች

- ለሃገርና ለእያንዳንዱ ክልል ብሎም አካባቢ የሚስማማ ከባባዊ የኢኮኖሚ መሰረትና የተፈጥሮ ሀብት ግምት ውስጥ ያስገባ የስልጠና ዓይነት ማደራጀትና የትብብር ስልጠና ሥርዓት መዘርጋት፤

- በህብረተሰቡና በተጠቃሚው ስለቴክኒክና ሙያ ያለውን የተሳሳተ አመለካከት ለመቀየር የሚያስችልና የዘርፉን ገፅታ ሊገነባ የሚያችል ስትራቴጂ መቅረፅና መተግበር፤

- በሁሉም አካባቢዎች ለሁሉም ዜጎች ፍትሃዊ ተደራሽነትን በሚያረጋግጥ መልኩ አግባብነት ያለውና ጥራቱን የጠበቀ የቴ/ሙ/ት/ሥ ስትራቴጂ መዘርጋት፤

- የኢንዱስትሪዎችና የዘርፍ ባለሙያዎች ሙሉ ተሳትፎ የተረጋገጠበት የሙያ ደረጃ ማዘጋጀትና አሁን ያለውን ሙያ ደረጃ መከለስ፤

## ስትራቴጂ ጋር የተያያዙ . . .

- በተለያየ የትምህርት እርከን (ከቅድመ መደበኛ ትምህርት እርከን በመጀመር) የአካዳሚክና የተግባር /ቴክኒክ/ ምጣኔ ግምት ውስጥ ያስገባ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል እስትራቴጂና አሰራር ማዘጋጀት፤
- ተግባር ተኮር ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል የተለያዩ የኢንዱስትሪና የተግባር ልምድ ግምት ውስጥ ያስገባ የስልጠና ሞዴል መከተል (ለምሳሌ፡- አፓረንቲስሽፕ፣ የመማሪያ ፋብሪካ . . . )፤
- የስልጠና መሠረተ ልማት እጥረትና የበቁ አሰልጣኞች እጥረት ላይ ያለው ክፍተት ለመሙላት የተቀናጀ የወርክሾፖችና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፣
- ብቁ እና ልምድ ያላቸው አሰልጣኞች ለመሳብ፣ ለመመልመልና ለማልማት የሚያስችል ስትራቴጂ ማዘጋጀት፤

# ከአደረጃጀርና አመራር ጋር የተያያዙ ለውጦች ምክረ ሀሳቦች፡-

- ተገቢ፣ ብቁ እና አቅም ያለው መደበኛ፣ መደበኛ ያልሆነ እና ኢ–መደበኛ ቴ/ሙ/ት/ሥ እና የተግባረ እድ ልማት የሚያስተዳድርና የሚመራ  ተቋም በሚንስቴር ደረጃ ማቋቋም፤
- በሃገር ፣ በክልል ፣ በዞን ፣ ወረዳ እና በከተማ ደረጃ ጠንካራና ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ አደረጃጀትና አመራር መፍጠር፤
- አለም አቀፍ ተሞክሮ መሠረት በማድረግ የባለሙያዎች አለምአቀፍ ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የባለሙያዎች የብቃት መመዘኛ ማዕከል /COC/ ማደራጀት፤
- ለሁሉም ለአጭርና መካከለኛ የቴክኒክና ሙያ የስልጠና እርከኖች ሥርዓተ ትምህርትና የስልጠና መጻሕፍት የሚያዘጋጅ ሃገራዊ ማዕከል ማደራጀት፤

# ከአደረጃጀርና አመራር . . .

- የፖሊሲ ሃሳብ የሚያመነጭና የየወቅቱን ሁኔታዎች በማጥናት የፖሊሲ ሃሳቦች ለመንግሥት የሚያቀርብ የቴ/ሙ/ት/ሥ/ ምርምር ተቋም ማቋቋም፤
- በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እንዲደጋገፉ የክላስተር አደረጃጀት መፍጠር፤
- የሙያ ስታንዳርድ፡ የሙያ ስልጠና ሥርዓተ–ሥልጠና እና የክህሎት ምዘና ዘዴ (assessment instruments) የሚያዘጋጅ ብሔራዊ የየዘርፉ የሙያ ምክር ቤት (National Sector Skill Councils) ማቋቋም፤

# ከስልጠና አቅርቦት ጋር በተያያዘ የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች

**የስልጠና ተቋማት በተመለከተ**

- መደበኛ የቴ/ሙ/ት/ሥ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (በደረጃ 1 እና 2) እና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ሥልጠና (ደረጃ 3 እና ከዚያ በላይ) የሚያሰለጥኑ ተቋማት አድርጎ ማደራጀት፤

- መደበኛ ያልሆነውን የቴ/ሙ/ት/ሥ  እና የክህሎት ሥልጠና ፕሮግራም በመሠረታዊ የቴ/ሙ/ት/ሥ ማዕከላት እና በልዩ ሁኔታ በተደራጁ የቴ/ሙ/ት/ሥ  ተቋማት  ለመሰረታዊ ክህሎትና ልዩ ልዩ መካከለኛ የኢንዱስትሪ ሙያተኞች (ከደረጃ 1 – 5)፤ ማሰልጠን በሚያስችል መልኩ ማደራጀት

- ከፍተኛ ቴክኒሻኖች፣ ቴክኒካል መሐንዲሶችና ማስተር ቴክኖሎጂስቶች የሚያሰለጥኑ ከፍተኛ ቴ/ሙ/ት/ሥ ዩንቨርስቲዎች ማቋቋም፤

# ከስልጠና አቅርቦት. . .

- በቀጠናውና በዓለም የሙያተኛ ገበያ ተወዳድረው መቀጠር የሚችሉ ወጣቶችን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ማቋቋም፤

# ከስልጠና አቅርቦት. . .

**<u>የስልጠና ቁሰቁስ በተመለከተ</u>**

- የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቀማት ብቁ የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል ቁሳቁስ፡ አሰልጣኞች እና አመራር እንዲማሉ ማድረግ፤
- የቴክኒክና ሙያ ተመራቂዎች ሥራ ፈጣሪ ሆነው ሊወጡ የሚያስችል የኢንተርፕራይዞች መፈልፈያ ማዕከል /Incubation center/ ማደራጀት
- የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች በአካባቢያቸው የተግባር ልምምድ ለማድረግ የሚያስችል ኢንዱስትሪ በሌለበት ሁኔታ በማሠልጠኛ ተቋም ውስጥ የመማሪያ ፋብሪካ /learning factory/ ማደራጀት፤

# ከስልጠና አቅርቦት. . .

**<u>አሰልጣኞችን በተመለከተ</u>**

- ብቁና የኢንዱስትሪ ክህሎት ያላቸው አሰልጣኞችን ለመሳብ የሚያስችል የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤
- በተመረጡ የቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጆችና እና የቴ/ሙ/ት/ሥ – ቴክኒካል ዩንቨርቨርስቲዎች  የቴክኒክና ሙያ መምህራን ማሰልጠን እንዲችሉ ማደራጀት፤

**<u>የብቃት ምዘና በተመለከተ</u>**

- የሙያ ማህበራት፤ የግሉ ዘርፍና የንግድ ምክር ቤቶች የሙያ ምዘና እስታንዳርድ መመዘኛ መሳርያ ዝግጅትና በምዘና እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- ሰለጣኞች የውጤት አሰጣጥ ሥርዓት "የበቃ" "ያልበቃ" ከማለት በቁጥር የሚገለፅ ውጤት (grade) መስጠት፤

## ➢ ከገፅታ ከመገንባት አንፃር የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች፡-

- የቴ/ሙ/ት/ሥ አቅም (ጥቅም፡ ሥፋትና ጥልቀት) በፖሊሲ አመንቺዎች፡ በአስፈጻሚዎች፡ በማሕበረሰቡ፡ በወላጆችና በተማሮወች ዘንድ የሚያስተዋውቅ ብሔራዊ/ሀገራዊ ፕሮግራም (promotion program) መፍጠር፤

- በመካከለኛ እና በከፍተኛ ሙያ እርከን ማለትም በሰለጠነ ሰራተኛነት፣ ቴክኒሻን ፣ ቴክኖሎጂስት፡ ወዘተ ማሰልጠን የሚችሉ ምርጥ እና ለስልጠና አመቺ ድባብ መፍጠር የሚችል የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት (brand residential separate TVET institutions) መገንባት፤

## ከገፅታ ከመገንባት አንፃር የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች.....

- የሰልጣኞች አቅምና ውጤት መሠረት ያደረገ የተለያየ የቅበላ መመዘኛና የስልጠና ሥርዓት በመዘርጋት ተወዳዳሪ ሰልጣኞች መሳብና ማሰልጠን እንዲቻል፡ - ሁሉምን ስልጠኝ በጀማሪ ሰልጣኝ (በደረጃ 1 ስልጠና) ከመቀበል ይልቅ እንደ ትምህርት ደረጃቸው ለሚመጥናቸውን የስልጠና እርከን መቀበል፤
- ተማሪዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸው ጀምሮ የቴክኒክና ሙያ እውቀትና ፍላጐት እንዲያድርባቸው በሥርዓተ-ትምህርቱ የቴክኒክ/vocational/ ይዘት ባካተተ መልኩ መቅረፅ፤
- በሁለተኛና በድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ደረጃ መስጠት በሚያስችል ሁኔታ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናን ማደራጀት፣
- ለቴ/ሙ/ት/ሥ ሁለተኛ ደረጃ ምሩቃን ለደረጃቸው የሚመጠን የክህሎት ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ማድረግ፤

# የቴ/ሙ/ት/ሥ ዘርፍ በፋይናንስ ከማጠናከር አንፃር የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች

- ፌዴራልና የክልል መንግስታት ቴክኒክና ሙያ ፋይናንስ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት /ፎርሙላ/ ማዘጋጀት፤
- አለም አቀፍ የልማት አጋሮችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቴክኒክና ሙያ በፋይናንስ ለማጠናከር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤
- እንዱስትሪዎችና የቢዝነስ ተቋማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት የስልጠና ፈንድ ማቋቋም፤
- የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በራሳቸው አቅም የፋይናንስ ገቢያቸው የሚያሳድጉበት ሥርዓት መዘርጋት፤
- ለቴክኒክና ሙያ ተቋማት አፈፃፀም/ብቃት/ መሠረት ያደረገ የፋይናንስ ማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤

አመሰግናለሁ!